በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር - 226785

ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

በዕዉቀት በላይ

ተሾመ ሽፈራዉ

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች፡-** ናሽናል አይል ኢትዮያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቆች ዶ/ር ነዋይ እና አቶ አለማየሁ ተፈራ- ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር (በቀድሞ የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ ባለ ስልጣን)- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍርድ**

ጉዳዩ የሸማቾች ጥበቃ አዋጅን መሠረት በማድረግ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩ በተጀመረበት በባለስልጣኑ (የተጠሪ) የዳኝነት ችሎት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበዉን ክስ መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

ተጠሪ ለባለ ስልጣኑ የዳኝነት ችሎት ያቀረበዉ ክስ ይዘትም በአጭሩ አመልካች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ከግዮን ጋዝ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እውቅናና ፍቃድ ውጪ ጂጂሲ (GGC)፤ ጂጂሲ ጊዮን ጋዝ ፒኤልሲ (GGC Ghion Gas PLC) እና ዋይ ፒ ሲ ታም (YPC TAM) የሚል በአእምሯዊ ንብረት ጽህፈት ቤት የተመዘገበ የንግድ ምልክት ያላቸው ቀይ የሆኑ ሲሊንደሮች ውስጥ ከውጪ ያመጣውን ጋዝ በመሙላት ለገበያ አቅርቦ በመሸጥ፤ በሲሊንደሮች ማሸጊያ ላይ ሸማቹ ሊለየው በማይችል ሁኔታ ኖክ (NOC) የሚል

አነስተኛ የፕላስቲክ መጠቅለያ በማድረግ የሚያደናግር ተግባር ከመፈፀሙም በተጨማሪ የግዮን ጋዝ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ንብረት የሆኑትን የተለያዩ ሲሊንደሮች በድርጅቱ ውስጥ በብዛት በማከማቸት ውድድርን የሚያጠፉ ተግባራት በመፈጸም የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 8 ድንጋጌ የተላለፈ ስለሆነ በአዋጁ አንቀጽ 42(3) መሰረት የ10% አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲጣልበት ይወሰንልን የሚል ነዉ፡፡

አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ መልስ ለግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተሰጠው የንግድ ምልክት ከውጭ ሀገር እያስመጣና በተለያየ ሲሊንደር እየሞላ መሸጥ በሚል የአገልግሎት ዘርፍ የስራ ምድብ 35 እና 37 እንጂ ለምርቱ፣ ለጋዝ አሞላል ስርዓት፣ ለሲሊንደሩ ወይም ሲሊንደሩ ለሚኖረው የቀለም ቅንብር፣ ለሲሊንደሩ ኢንዱስትሪ ንድፍ፣ ለተሰራበት ቁስ ወይም መጠን አይደለም፡፡ ግዮን ጋዝ በብቸኝነት እንዲጠቀማቸው በስሙ የተመዘገቡ አይደሉም፡፡ በውጪ አገር የሲሊንደር አምራቾች ውክልና አግኝቶ ኢንዱስትሪያል ንድፍን በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ጽ/ቤት አስመዝግቦ ጥበቃ እስካላገኘ ድረስ ሲሊንደሮቹ በህዝብ ባለቤትነት ስር (Public domain) ስለሚሆኑ ማንኛውም ሰው ሊጠቀምባቸው የሚችል ሲሆን፣ ቀይ ቀለም በመቀባቱና ምልክቶቹን በሲሊንደሩ ላይ በማድረጉ በብቸኝነት የመጠቀም መብት አይሰጠውም፡፡ አመልካች የሚቀርቡለትን ባዶ ሲሊንደሮች ቡታጋዝ ሞልቶ ያስረክባል ወይም ያከፋፍላል እንጂ ባዶም ሆነ ጋዝ የተሞላ ሲሊንደር ሸጦ አያውቅም፤ ሲሊንደር ወስዶ አይሞላም፤ አይሸጥምም፡፡ ደንበኞች መያዥያ ሰጥተው የወሰዷቸውን ባዶ ሲሊንደሮች ሲቀርቡለት ብቻ ቡታ ጋዝ ይሞላል፡፡ የግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሆኑ ሲሊንደሮችን ቀርቶ የራሱን ሲሊንደሮች እንኳን ለተጠቃሚው የሚያስተላልፈው በሽያጭ ሳይሆን የተወሰነ ብር በማስያዝ እንዲጠቀሙበት በነፃ ነው የሚሰጣቸው፡፡ አመልካች እንኳን የሌላውን ተወዳዳሪ ድርጅት ባዶ ሲሊንደር ይቅርና የራሱን ሲሊንደሮች አይሸጥም፡፡ አመልካች ለሸማቹ ማህበረሰብ ተደራሽ የሚያደርጉ ቡታ ጋዝ አከፋፋዮች ጋዝ ለማስሞላት ወደ ኩባንያችን ይዘዋቸው የሚመጡትን ሲሊንደሮች የግል ንብረቶቻቸው ወይም የደንበኞቻቸው መሆናቸውን በቃል ወይም በጽሁፍ ሲያረጋግጡልን ብቻ ቡታ ጋዝ ሞልተን የጋዙን ዋጋ ብቻ ማስከፈሉ ጂጂሲ (GGC) ጂጂሲ ጊዮን ጋዝ ፒኤሲ (GGC Ghion Gas PLC) እና ዋይፒሲ ታም (YPC) የሚለውን ምልክት ያላግባብ ተጠቅሟል ሊያስብል አይችልም፡፡ ደንበኞች ከልምድ እና ከግንዛቤ አንጻር ስለምርቱ ያላቸው ንቃተ ህሊና ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑ ምርቱን ሲገዙ ለመለየት አይቸገሩም፡፡ ሲሊንደሮቹ የሚመረቱት ጀሀገር ውጪ በመሆኑና በሀገራችን ሲሊንደሮች ለማምረት የሚያስችል ቴክኖሎጂ ስለሌለ አመልካች ማሸጊያውን በማስመሰል ህብረተሰቡን የሚያሳስት ተግባር ሊፈጸም አይችልም፡፡ የግዮን ጋዝ ከደንበኞች ጋር ውል እንዳለው ይገመታል፣ መያዥያ አሲዞ በተለየ ውል መነሻነት ለሸማቾች ተላልፎ ከሆነም ተከሳሽ በጊዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና በደንበኞቹ መካከል ያለውን የግል ግኑኝነት ስለማያውቅ እና የጣሰውም ውል ስለሌለ ሊጠየቅ የሚገባው ሸማቹ እንጂ በሸማቹ ጥያቄ አቅራቢነት ሲሊንደሮቹን ፈሳሽ ቡታጋዝ የሞላው ተከሳሽ ሊሆን አይገባም፡፡ አመልካች የግዮን ጋዝ የሆኑትን ሲሊንደሮች ማሸጊያ እያሸገ ሸጠ እንጂ ተጠሪ እንደሚለው በማሸጊያው (ካፕ) ላይ ሸማቹ ህብረተሰብ ሊለየው በማይችለው ሁኔታ NOC በሚል አነስተኛ ፕላስቲክ መጠቅለያ እያሸገ ለገበያ በማቅረብ ሸማቹን ህብረተሰብ የሚያደናግር ተግባር ፈጽሞ አያውቅም፡፡ “ኖክ” የሚለው ማሸጊያ ከላዩ ላይ ባለው ስያሜ፣ የማሸጊያ ቅርጽ፣ እላዩ ላይ ባለው ስያሜ እና በጊዮን ጋዝ ማሸጊያ ላይ ባለው ቅንብር መካከል ምንም አይነት የድምጻሜ፣ የቃላት አደራደር፣ የፊደል አፃፃፍ እና ማሸጊያው ላይ ባለው ቅርፅ የከለር ቅንብር ምንም አይነት መመሳሰል ባለመኖሩ ሸማቹ በቀላሉ ሊለያቸው የሚችል ነው፡፡ ሀሰተኛ/አሳሳች/ ሊሆን ይችል የነበረው ተከሳሽ ከውጭ ሀገር የሚያስመጣቸውን በህዝብ ባለቤትነት በተያዘው ሲሊንደር ውስጥ እየሞላ በአናቱ ላይ በከሳሽ ድርጅት ማሸጊያ ሲሸጥ ቢገኝ ወይም የተሞላ ጋዝ ለተገቢው አገልግሎት የማይውል ቢሆን ነበር በማለት ተከራክሯል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት በአመልካች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ውድቅ ካደረገ በኃላ ግራ ቀኙን በማከራከር የቀረቡ ምስክሮች እና ማስረጃዎችንም በመመርመር ደንበኞች ምርቱን የገዙት አመልካች ድርጅት ሳይሆን ከሱቆች ነው፤ የጊዮን ጋዝ ሊገዙ ሄደው ተሳስተው የናሽናል ኦይል ምርት ገዝተው ከሆነ አሳስቶ የሸጠላቸው አመልካች ሳይሆን የሸጠላቸው ሱቅ ነው፤ በሌላ በኩል ጊዮን ጋዝ ሲሊንደሮቹን እንዲጠቀሙና ተመልሰው ከሱ እንዲጠቀሙ በሚያስሩት ውል መሰረት የሽያጭ ውል ስራውን እንደሚያከናውን የተካደ ጉዳይ አይደለም፤ አንድ ደንበኛ ውሉን በመተው ወደ ሌላ ድርጅት ከሄደ ጉዳዩ መፈታት ያለበት በውል ህግ እንጂ የውል አካል ያልሆነው 3ኛ ወገን ለምን የእኔን ደንበኛ ትቀበላለህ ተብሎ መጠየቅ ተገቢ አይደለም፤ የተጠሪ ክስ ይዘት አመልካች በግል ተበዳይ የጋዝ ሲሊንደር ላይ ናሽናል ኦይል የሚል እየለጠፈ ስለሚሸጥ ሸማቹን የሚያደናግር ተግባር ፈጽሟል የሚል ነው፤ ሆኖም አመልካች ይህንን ማድረጉ ባቀረባቸው ማስረጃዋች አላስረዳም፡፡ የግል ተበዳይ አመልካች የእኔን ሲሊንደሮች ተጠቅሟል የሚል ከሆነ ይህ ጉዳይ መታየት ያለበት ከንብረት ባለቤትነት ጋር ተያይዞ በሌላ ህግ ነው፡፡ የግል ተበዳይ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ጋዝ ከውጭ አስመጥቶ በሲሊንደር ሞልቶ የመሸጥ የቃል ጥበቃ በኢትዮጵያ አእምራዊ ንብረት ጽ/ቤት እንደተሰጠው የሚገልጽ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ከክሱ ጋር በማስረጃነት አያይዞ አቅርቧል፡፡ የቀረበው ማስረጃ ለግል ተበዳይ የተደረገለት ጥበቃ የቃል የሚል ሲሆን ይህ ማለት ደግሞ ለግል ተበዳይ የተደረገለት ጥበቃ ግዮን ጋዝ ለሚለው ነው፡፡ ይህ ጥበቃ አመልካች ከሚጠቀምበት ናሽናል ኦይል ጋር የሚያመሳስለው ነገር የለም፤ ሸማቾችንም አያደናግርም፡፡ ጥበቃ ከተደረገለት የንግድ ምልክት ጋር የማይመሳሰሉ ከሆነ ደግሞ የወል ወይም የጋራ መጠቀሚያ በሆነው ዕቃ ተጠቅሞ ምርቱን ለገበያ ማቅረብን አዋጁ የሚከለክል አይደለም በሚል ክሱን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ ለፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ ሸማቾች ጋዙን የገዙት ከሱፐር ማርኬት ወይም ጋዝ ከሚሸጥበት ድርጅት መሆኑን በጊዮን ጋዝ ሲሊንደር ላይ የተሞላው እና የተሸጠው ጋዝ በናሽናል ኦይል አልተሞላም ሊያስብል አይችልም፤ በአመልካች ቀርቦ የነበረው ክርክር በጊዮን ጋዝ ሲሊንደር አልሞላንም ሳይሆን ንብረትነቱ የአከፋፋዮቹ/የደንበኞች/መሆኑን እያረጋገጥን የራሳችንን አርማ (NOC) በኪዳኑ ላይ እያስቀመጥን ለአከፋፋዮች በሲሊንደሩ ጋዝ እየሞላን ሸጠናል ነው፡፡ ሸማቹ ደግሞ ጋዝ የሚገዙት ከእነዚህ አከፋፋዮች መሆኑ እየታወቀ እና በመልስ ሰጪ በኩል የቀረቡት የፎቶ ግራፍ እና የኤግዘቢት ማስረጃዎች እያመላከቱ ተከሳሽ እንዳልተመሰከረበት የተደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ አይደለም፡፡ የሲሊንደር ጋዝ ሽያጭ ሂደት ደግሞ ሸማቹ ጋዝ ከሚሞሉ ድርጅቶች በውል እና በመያዣ ያገኙትን ሲሊንደር ወደ ሲሊንደር መሸጫ ቦታ ወይም የጋዝ መሸጫ ድርጅት በመሄድ በያዙት ባዶ ሲሊንደር ምትክ ተመሳሳይ የተሞላ ሲሊንደር ከመሸጫ ቦታ ገዝቶ መሄድ መሆኑ እየታወቀ እና ይሄንኑ ተጠሪ በማስረጃ አስደግፎ እያለ ጋዙ በማን እንደተሞላ አልተመሰከረም መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ እንዲሁም የውሀና ኢነርጂ ሚንስቴር ስለቡታጋዝ አጠቃቀም በስሩ ላሉ የንግድ ድርጅቶች በጻፈው ደብዳቤ አንዱ በሌላው ሲሊንደር ላይ ጋዝ እየሞላ እንዳይሸጥ የከለከለ ሆኖ እያለ አመልካች የግል ተበዳይ ስሊንደር ላይ ጋዝ ሞልቶ በራሱ እስቲከር አሽጎ ለአከፋፋዮች መሸጡ ተረጋግጦ እያለ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየዉ የባለስልጣኑ የዳኝነት ችሎት የተጠሪን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ የንግድ ምዝገባ ጥበቃ አዋጅ 501/98 እና የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ 813/2006ን አላማ ያላገናዘበ ነው በማለት ሸሮ አመልካች ከ 2012 ዓ.ም በጀት አመት ከሲሊንደር ጋዝ አመታዊ ሽያጭ ላይ ብቻ 5% እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅሬታ ያቀረበ ቢሆንም፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የፌዴራል የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች ግንቦት 15 ቀን 2014 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ የሰበር አቤቱታውም የሥር ይግባኝ ሰሚው የአስተዳደር የዳኝነት ችሎት የጹሑፍ መልስ የማቅረብ መብቴን አላግባብ ነፍጎኝ በፈጸመው የሥ/ሥርአት ሕግ ግድፈት ላይ ቅሬታው የቀረበለት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምንም ሳያነሳና እርምት ሳያደርግባቸው ማለፉ አግባብ ባለመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎት ተገቢ ነው የሚለውን ማረሚያ እንዲሰጥበት፤ ሸማቾች እራሳቸው ጋዝ እንዲሞላላቸው ባቀረቧቸው ሲሊንደሮች ላይ ጋዝ ሞልቶና አሽጎ መሸጥ የሚያደናግር ተግባር ነው በሚል ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተፈጽሟል በማለት የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ አላግባብ ነው፤ የአሁን አመልካች GGC gas የሚል የንግድ ምልክት ባለባቸው ሲሊንደሮች ላይ ጋዝ እየሞላና እያሸገ ስለመሸጡ በስር የዳኝነት ችሎት ያልተረጋገጠን ጉዳይ የጠቅላይ ፍ/ቤት እንደተረጋገጠ አድርጎ የሰጠው ውሳኔ አግባብ ባለመሆኑ እንዲታረምልኝ፤ የውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ለተወሰኑ የንግድ ድርጅቶች የራሳቸው ባልሆነ ሲሊንደር ላይ ጋዝ እንዳትሞሉ በማለት በጽሁፍ ያስተላለፈው ትእዛዝ በመመሪያነት ሊወሰድ የሚችል ካለመሆኑም በላይ የሸማቹን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የወጣውን አዋጅ 813/2006 የሚተላለፍ ነው በማለት ፍርድ እንደያርፍበት እና ይግባኝ ሰሚ የአስተዳደር ዳኝነት ችሎት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ወሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት ጠይቋዋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአሁን አመልካች በግዮን ጋዝ ሲሊንደሮች የራሱን ጋዝ እየሞላ እና የራሱን ስም (NOC) በሚል በማሸግ መሸጡ የግዮን ጋዝ ከሚያቀርበው አገልግሎት ጋር ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተግባር ፈጽሟል በማለት የጥፋተኝነትና ቅጣት ውሳኔ የተሰጠበት አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 813/06 አንቀጽ 2(9)፣8፣14 እና ከአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 26 መሰረት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህ መሠረት ተጠሪ ታህሳስ 05 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ መልስ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ጸንቶ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አመልካችም አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ በአጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ ተጠሪ ለስር የዳኝነት ችሎት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ አመልካች ከጊዮን ጋዝ ድርጅት ዕዉቅናና ፈቃድ ዉጪ ሸማቹን ማህበረሰብ በሚያሳስት እና በሚያደናግር ሁኔታ የጊዮን ጋዝ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሆኑ ቀለማቸዉ ቀይ የሆኑና በኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ጽ/ቤት ያስመዘገባቸዉንና ጥበቃ የተደረገላቸዉን GGC, GGC GHIon, Gas PLC እና YPC TAM የተባሉ ሲሊንደሮች ዉስጥ አመልካች ከዉጭ የሚያመጣዉን ጋዝ በመሙላት ለገበያ አቅርቦ መሸጡንና በማሸጊያዉም ሸማቹ ህብረተሰብ ሊለየዉ በማይችለዉ ሁኔታ NOC በሚል አነስተኛ ፕላስቲክ መጠቅለያ እያሸገ ለገበያ በማቅረብ ሸማቹን ህብረተሰብ የሚያደናግር የተወዳዳሪ ጥቅም የሚጎዳ ተግባር ፈጽሟል የሚል ምክንያት በመጥቀስ ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ለጊዮን ጋዝ የተሰጠዉ ጥበቃ የቃል ነዉ፣ ለጋዙ አሞላል ስርዓት ወይም የስሊንደሩን የቀለም ቅንብር አስመልክቶ የተሰጠዉ ጥበቃ የለም፣

አመልካች ደንበኞች በሚያመጡት ሲሊንደር ጋዝ ሞልቶ ከማስረከብ ዉጪ ሲሊንደሮችን ሸጦ እንደማያዉቅ፣ አብዛኛዎቹ የአመልካች ደንበኞች ንቃተ ህሊናቸዉ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ ሌሎች ተጠቃሚዎችም ቢሆኑ ማሸጊያዉ በቀላሉ በሚታይ ቦታ የሚሞላ በመሆኑ ጋዙ በማን እንደተሞላ ሲገዙም ሆነ ሲጠቀሙበት ለመለየት የማያስቸግር በመሆኑ አመልካች ህብረተሰቡን የሚያሳስትና የሚያደናግር ተግባር ፈጽሟል የሚያስብል ሁኔታ አለመኖሩን ጠቅሶ መከራከሩን ነዉ፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ችሎት ከላይ የተገለጸዉን ምክንያት በመጥቀስ የተጠሪን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ያደረገ ቢሆንም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በበኩሉ በስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮ እና መዝኖ አመልካች ስሊንደር ለሸማቾች የሚሞላበትን ሁኔታ አስመልክቶ ያቀረበዉን ክርክር በማስረጃ አለማረጋገጡን፤ የአመልካች ክርክር በጊዮን ጋዝ ስሊንደር አልሞላም የሚል ሳይሆን አርማዉን በክዳኑ ላይ በማሸግ ለአከፋፋዮች መሸጣቸዉን ሲሆን፣ ሸማቾች ደግሞ ጋዝ የሚገዙት ከአከፋፋዮች ስለመሆኑ በፎቶግራፍ እና በኤግዝቢት መረጋገጡን፤ የተጠሪ ምስክሮች የጊዮን ጋዝ ደንበኞች መሆናቸዉንና የጊዮን ጋዝ መግዛት ፈልገዉ በስሊንደር ገዝተዉ እቤታቸዉ ከደረሱ በኋላ ስሊንደሩ GGC ቢልም በክዳኑ ላይ ናሽናል ኦይል የሚል ማሸጊያ አይተዉ ለጊዮን ጋዝ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ደዉለዉ እዉነታዉን እንዳሳወቁ እና የመጠን ማነስም እንደገጠማቸዉ ማስረዳታቸዉን፤ የስሊንደር ጋዝ ሽያጭ ሂደት ደግሞ ሸማቹ ጋዝ ከሚሞሉ ድርጅቶች በዉል እና በመያዣ ያገኙትን ስሊንደር ወደ ስሊንደር መሸጫ ቦታ ወይም የጋዝ መሸጫ ድርጅት በመሄድ በያዙት ባዶ ስሊንደር ምትክ ተመሳሳይ የተሞላ ስሊንደር ከመሸጫ ቦታ ገዝቶ መሄድ ስለመሆኑ መረጋገጡን፤ ስለ ቡታ ጋዝ አጠቃቀም አስመልክቶ ከዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ ደብዳቤ እያንዳንዱ ኩባኒያ በራሱ ስሊንደር ብቻ ጋዝ እየሞላ መሸጥ እንዳለበት ይህ ካልሆነ ህጋዊ እርምጃ እንደሚወስድ ማሳሰቡን አረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት አመልካች ኃላፊነት አለበት በሚል የወሰነዉም በፍሬ ነገር ደረጃ በዚህ መልኩ የተረጋገጠዉን መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይህንኑ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ተቀብሎታል፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) እንዲሁም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀ ጽ 2(4) እና 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ በመሆኑ፣ ከላይ በተመለከተዉ ሁኔታ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር ትክክለኛነት በድጋሚ ለመመርመር የሚያስችል ስልጣን የለዉም፡፡

እንግዲህ ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ባላቸዉ ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ከላይ የተመለከተዉ ከሆነ፣ በህግ ረገድ የሚያስከትለዉ ዉጤት ምንድን ነዉ? የሚለዉን ነጥብ እንደሚከተለዉ እንመለከታለን፡፡ እንደሚታወቀዉ የተለያዩ ሀገራት ለንግድ ዉድድር ህጎችን ወይም ፖሊሲዎችን የሚያወጡባቸዉ ወይም የሚቀርጹባቸዉ ዓላማዎች እንደየአገራቱ ታሪክ፣ የፖለቲካ አስተዳደር ስርዓት፣ መንግስት በኢኮኖሚዉ ዉስጥ ያለዉን ወይም ሊኖረዉ በሚገባዉ ድርሻ ላይ የሚመሰረት በመሆኑ በተወሰነ ደረጃ የሚለያይ ቢሆንም፤ በአብዛኛዎቹ አገራት ለማለት ይቻላል፣ የንግድ ዉድድር ህጎች ዓላማ ተብለዉ የሚወሰዱት የሸማቾችን ደህንነት ማስጠበቅ፣ የኢኮኖሚ አፈፃፀም ማሻሻል፣ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ማድረግ ስለመሆኑ በዙሪያዉ የተፃፉ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡ የንግድ ዉድድር ህጎች አጠቃላይ ዓላማ እና ግብ ግብይቶች ፍትሐዊ በሆነ የዉድድር ሥርዓት እንዲመሩ ማድረግ ስለመሆኑም የሚታወቅ ነዉ፡፡ በአገራችን በ2013 ዓ.ም የወጣዉ የንግድ ዉድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 ዓላማም የንግዱን ህብረተሰብ ከፀረ-ዉድድር እና ተገቢ ካልሆነ የገበያ ተግባራት እንዲሁም ሸማቹን ከሚያሳስቱ የገበያ ሁኔታዎች በመከላከል ለነፃ ገበያ ዉድድር አመቺነት ያለዉን ሥርዓት ለማስፈን እና ተገቢ ያልሆነ የንግድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ዉድድርን ለመከላከል እንደሆነ በአዋጁ መግቢያ ላይ ከተመለከተዉ ሃሳብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አዋጁ ስለ *"ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር"* በሚያወሳዉ አንቀጽ 8 ንዑስ ቁጥር 1 ስር ማንኛዉም ነጋዴ በንግድ ሥራ ሂደት ዉስጥ ማንኛዉም ሀቀኛ ያልሆነ፣ አሳሳች ወይም አታላይነት ያለበት እና የተወዳዳሪን የንግድ ጥቅም የሚጎዳ ወይም ሊጎዳ የሚችል ድርጊት ነዉ በሚል የሚደነግግ ሲሆን፤ ተገቢ ያልሆኑ ተግባራት ምን ምን ናቸዉ ለሚለዉም ጥያቄ አዋጁ በአንቀጽ 8(2) ላይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በዚህም መሠረት ተገቢ ያልሆኑ ተግባራት ማለት ነጋዴዉ ከሚያቀርበዉ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ድርጊት፤ የሌላዉን ነጋዴ መረጃ ማዉጣት፣ መያዝና መጠቀም፤ ሌላዉን ነጋዴ የሚያሳጣ ማናቸዉም ሀሰት የሆነ ወይም ማረጋገጫ የሌለዉ አገላለጽ፣ በንግድ ማስተዋወቅ ስራ ሂደት የንግድ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በሐሰት ወይም በተዛባ ሁኔታ ማነፃፀር፣ ከንግድ ዕቃዎች ወይም ከአገልግሎቶች ዋጋ ወይም ባህሪ ወይም አመራረት ወይም ከማምረቻ ቦታ ወይም ከይዘት ወይም ከአጠቃቀም ምቹነት፣ ከጥራት ጋር በተገናኘ ምንጩ ያልታወቀዉን ጨምሮ ለሸማቾች ወይም ለተጠቃሚዎች ሀሰተኛ ወይም የተዛባ መረጃ ማሰራጨት እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡ ስለሆነም አንድ ሰዉ ከንግድ አካሄድ ጋር በተያያዘ ከእነዚህ ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ተግባር የፈጸመ መሆኑ ከተረጋገጠ በአዋጁ መሠረት ኃላፊነት አለበት፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች በጊዮን ጋዝ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር በሆኑ ስሊንደሮች የራሱን ጋዝ በመሙላት በኪዳኑ ላይ የራሱን ስም NOC በሚል በማሸግ ለአከፋፋዮች መሸጡ፣ ጋዙን ከአመልካች የገዙት ሸማቾችም ጋዙ የጊዮን ጋዝ ነዉ በሚል ገዝተዉ ቤት ከደረሱ በኋላ ኪዳኑ NOC የሚል ምልክት ባለዉ ጽሑፍ መታሸጉን በማየት እንዲሁም የመጠን መቀነስ መኖሩን ደርሰዉበት ለጊዮን ጋዝ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ደዉለዉ ያሳወቁ መሆኑ፣ እንዲሁም በሌላ ሰዉ ስሊንደር መጠቀም ኃላፊነትን እንደሚያስከትል ጉዳዩ በሚመለከተዉ በወቅቱ የዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተብሎ በሚታወቅ አካል የተፃፈዉ ደብዳቤ መኖሩ መረጋገጡ የሚያሳየዉ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 8(2) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ጥፋት መፈጸሙን ነዉ፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በማስረጃ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር እና ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉን ድንጋጌ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00048 ላይ ሰኔ 25 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 195450 ላይ የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !